የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20 እና 21

1. መግደላዊት ማርያም በጨለማ ወደ ጌታ መቃብር የሄደችው ለምንድን ነው?
ሀ)ከሙታን ተለይቶ እንደሚነሳ ስለምታውቅ መነሳቱን ልታይ
ለ)በዚያ ዘመን ሙታንን ሽቱ የመቀባት ሥርዓት ስለነበራቸው ጌታችንን ሽቱ ለመቀባት
ሐ)ሥጋውን ሌቦች ይሰርቁታል ብላ ስለፈራች አለመወሰዱን ልታረጋግጥ
መ)ሀ እና ሐ

2. ጌታችን መነሳቱን ለመግደላዊት ማርያም የነገራት ማን ነው?
ሀ)የአትክልት ሥፍራ ጠባቂው
ለ)የተገለጡላት መላእክት
ሐ)ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
መ)ስምዖን ጴጥሮስ እና ዮሐንስ

3. ማርያም መግደላዊት ጌታችን አለመኖሩን ከነገረቻቸው በኋላ ወደ መቃብሩ ከሮጡት ደቀመዛሙርት ወደ መቃብሩ የገባው የቱ ነው?
ሀ)ቅዱስ ጴጥሮስ
ለ)ቅዱስ ዮሐንስ
ሐ)መግደላዊት ማርያም
መ)ሁለቱም ወደ መቃብሩ ገብተዋል

4. ከጴጥሮስ ጋር ወደ መቃብር የሄደው ሐዋርያ ማን ነው?
ሀ)ዮሐንስ ለ)እንድርያስ ሐ)ናትናኤል መ)ያዕቆብ

5. ረቡኒ የሚለው ቃል ትርጓሜ ምንድን ነው?
ሀ)አባት ለ)መምህር ሐ)አትክልት ጠባቂ መ)መልስ አልተሰጠም

6. የዮሐንስ ወንጌል የተፃፈበት አላማ ምንድን ነው?
ሀ)የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሁሉንም ተአምራት ለመንገር
ለ) የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ከልደት እስከ እርገት እያንዳንዱን ነገር ለመንገር
ሐ)ሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌልን መፃፍ ስለፈለገ ብቻ
መ)ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንድናምን የዘላለምን ሕይወት እናገኝም ዘንድ

7. በምዕራፍ 21 ላይ ዓሣ ሊያጠምዱ ወደ ታንኳ ከገቡት ደቀመዛሙርት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ)ዮሐንስ ለ)ያዕቆብ ሐ)ዲዲሞስ መ)ፊልጶስ ሠ)ለ እና ሐ

8. ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ በጥብርያዶስ ባሕር ሲገለጥ በአጠቃላይ ከትንሳኤው ወዲህ ለስንተኛ ጊዜ ነው?
ሀ)ሦስተኛ ለ)አንደኛ ሐ)አራተኛ መ)ሁልጊዜ አብሯቸው ነበር

9. ጌታ ከማርያም መግደላዊት ካወጣቸው መናፍስት የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ)መንፈሰ ትዕቢት ለ)መንፈሰ ሐሜት ሐ)መንፈሰ ሐሰት መ)መልሱ የለም

10.ከሰዱቃውያን ወገን የሆነው ሐዋርያ ማን ነው?
ሀ)ማቴዎስ ለ)ዮሐንስ ሐ)ናትናኤል መ)ቶማስ

11. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ከትንሳኤው በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገለጥላቸው ስንት ነበሩ?
ሀ)11 ለ)10 ሐ)12 መ)13

12.ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20 ላይ ማን ተብሎ ተጠራ?
ሀ)ዲዲሞስ ለ)ናትናኤል ሐ)ቀልዮጳ መ)ስምዖን

13."ሰላም ለእናንተ ይሁን" የሚለውን የጌታችን ንግግር ዕለት ዕለት በምን ላይ እንሰማዋለን?
ሀ)በአባታችን ሆይ ጸሎት ላይ
ለ)በስርዓተ ማህሌት
ሐ)በቅዳሴ
መ)መልስ አልተሰጠም

14.በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ላይ ዓሳ ሊያጠምዱ የሄዱት እነማን ናቸው?
ሀ)ናትናኤል፣ ቶማስ፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ
ለ)ፊልጶስ፣ ቶማስ፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ
ሐ)ናትናኤል፣ ፊልጶስ፣ የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ
መ)ሁሉም

15.የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱ ዓሳ ሊያጠምዱ የሄዱት ወደ የትኛው ባሕር ነው?
ሀ)ወደ ጌንሳሬጥ
ለ)ወደ ገሊላ ባሕር
ሐ)ወደ ጥብርያዶስ ባሕር
መ)ለ እና ሐ

16.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱስ ጴጥሮስ እና በሱ ለሚተኩ አደራ የሰጠው ማንን ነው?
ሀ)እንስሳትን
ለ)እፅዋትን
ሐ)በስሙ የሚያምኑ አዛውንት ወጣቶች እና ሕፃናት
መ)መልስ አልተሰጠም

17. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱስ ጴጥሮስ "በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ ወገብህንም ሌላ ያስታጥቅሃል ወደ ማትወደውም ይወስድሃል " ሲለው ስለምን እየነገረው ነበር?
ሀ)ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ
ለ)ስለቅዱስ ጴጥሮስ ሞት
ሐ)ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
መ)ሁሉም

18.ከሚከተሉት ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱስ ጴጥሮስ ካለው ነገሮች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?
ሀ)ለፍርድ እስክመጣ ድረስ ሞትን አትቀምስም
ለ)የመንግስተ ሰማያትን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ
ሐ)ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የምታጠምድ አደርግሃለሁ
መ)አንተ አለት ነህ

19.ከሐዋርያት መካከል ሞትን ያልቀመሰው የቱ ነው?
ሀ)ጴጥሮስ ለ)ይሁዳ ሐ)ዮሐንስ መ)ሁሉም ሞትን አይተዋል

20. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ላይ ጌታ ጴጥሮስን "ግልገሎቼን ጠብቅ" ሲለው ግልገሎች የተባሉ እነማን ናቸው?
ሀ)12ቱ ሐዋርያት ለ)72ቱ አርድእት ሐ)36ቱ ቅዱሳት አንስት መ)ሁሉም

21.በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ላይ ጌታ ጴጥሮስን "ጠቦቶቼን አሰማራ" ሲለው ጠቦቶች የተባሉ እነማን ናቸው?
ሀ)12ቱ ሐዋርያት ለ)72ቱ አርድእት ሐ)36ቱ ቅዱሳት አንስት መ)ሁሉም

22. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ላይ ጌታ ጴጥሮስን "በጎቼን ጠብቅ" ሲለው በጎች የተባሉ እነማን ናቸው?
ሀ)12ቱ ሐዋርያት ለ)72ቱ አርድእት ሐ)36ቱ ቅዱሳት አንስት መ)ሁሉም